# ፍከሬ

## ኢየሱስ።

# ፍካሬ ፥
# ኢየሱስ ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ
ሥላሴ በ፴፫ኛው ዘመነ መንግሥት
፩ኛ ጊዜ ይህ መጽሐፍ
በተስፋ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፶፭ ዓ ፡ ም ፡

መን ፡ አይኖርም ፡ አንዱም ፡ አንዱን ፡
እንደ ፡ እውራ ፡ ይመለከታዋል ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ፡

### ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፲፬ ።

ለአሕዛብ ፡ ምስክር ፡ ይሆንባቸው ፡ ዘንድ
ይህ ፡ የመንግሥት ፡ ወንጌል ፡ በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ ይሰበካል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መጨ
ረሻው ፡ ይመጣል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ተጠ
ንቅቃችሁ ፡ ጠብቁ ።

### ማቴዎስ ፡ ፳፬ ፡ ፳፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡
ጀምሮ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያልሆነ ፡ ከእን
ግዲህም ፡ ከቶ ፡ የማይሆን ፡ ታላቅ ፡ መከ
ራ ፡ ይሆናል ፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ ላሉ ፡
ለርጉዞችና ፡ ነፍስ ፡ ጡሮች ፡ እንዲሁም ፡
ለአመጫዎችና ፡ ለሚያጠቡ ፡ ሁሉ ፡ ወዮ
ላቸው ፡ እነዚያ ፡ ቀኖችስ ፡ ስለደጋጎችና ፡
ስለተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ባያጥሩ ፡ ኖሮ ፡



ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ እንዳችም ፡ ባልዳ
ነም ፡ ነበር ፡ እንግዲህ ፡ ሽሽታችሁ ፡ በክ
ረምት ፡ ወይም ፡ በሰንበት ፡ እንዳይሆን ፡
ተግታችሁ ፡ ጸልዩ ።

## ትእዛዝ ፡ ጠብቁ ፡

### ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፫—፳፯ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ ክር
ስቶሶችና ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያቶች ፡ ይነሣ
ሉና ፡ ማንም ፡ እነሆ ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡
አለ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ነው ፡ ቢሏችሁ ፡
አትመኑ ፡ ብዙ ፡ ድንቅና ፡ ታላላቅም ፡
ምልክት ፡ በማሳየት ፡ የተመረጡትን ፡
ለማሳት ፡ ይሞክራሉ ። እንግዲህ ፡ እነሆ ፡
አስቀድሜ ፡ ነገርኋችሁ ፡ ክርስቶስ ፡ በበ
ርሀ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በእልፍኝ ፡ አለ ፡
ቢሏችሁ ፡ አትቀበሏቸው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡

እመጣጥ ፡ መብረቅ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወጥቶ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ እንደሚታይ ፡ ነውና ፡

**በዚያን ፡ ሰዓት ፡ ተጠንቀቁ ።**

**ማቴዎስ ፡ ፳፬ ፡ ፴፪—፴፭ ።**

ምሳሌውን ፡ ከበለሲቱ ፡ ተማሩ ፡ ጫፏ ፡ ሲያቆጠቁጥ ፡ ቅጠሏም ፡ ሲለመልም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጊዜው ፡ እንደቀረበ ፡ ትረዳላችሁ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስታዩ ፡ በደጅ ፡ እንደደረሰ ፡ ዕወቁ ፡ ዕውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም

**ማቴዎስ ፡ ፳፬—፴፮ ።**

ስለዚያች ፡ ቀንና ፡ ስለዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ ከአባት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ ልጅም ፡ ቢሆን ፡ የሚያ



ውቅ ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ነቅታችሁና ፡ ተግታችሁ ፡ ተዘጋጅታችሁና ፡ ተሰናድታችሁ ፡ ጠብቁ ።

**ማቴዎስ ፡ ፳፬ ፡ ፵፪ ።**

ከዚያም ፡ ወራት ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡ ፀሐይ ፡ ይጨልማል ፡ ጨረቃም ፡ ብርሃኗን ፡ አትሰጥም ፡ ከዋክብትም ፡ ከሰማይ ፡ ይወድቃሉ ፡ የሰማዮችም ፡ ኃይላት ፡ ይናወጣሉ ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ ይታያል ፡ የምድር ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ፡ የሰው ፡ ልጅንም ፡ በታላቅ ፡ ኃይልና ፡ በብዙ ፡ ክብር ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡ ሲመጣ ያዩታል ፡ መላእክቱንም ፡ በታላቅ ፡ የመለከት ፡ ድምፅ ፡ ጋር ፡ ይልካቸዋል ።

**ማቴዎስ ፡ ፳፬ ፡ ፳፱ ።**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከፀመሰና ፡ ከተንኮል ፡ የተነጣ ፡ በምድር ፡ ባለ ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታ ፡ የለም ። የኔን ፡ ገናንነት ፡ አላወቁምና ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደኔ ፡ ቢመለሱ ፡ ንስሐ ፡ ቢገቡ ፡ እኔም ፡ ይቅር ፡ እላቸዋለሁ ። ወደኔ ፡ ግን ፡ ባይመለሱ ፡ እኔም ፡ ፊቴን ፡ ከርሳቸው ፡ እመልሳለሁ ። ኤሳው ፡ ብኩርናውን ፡ ለመብል ፡ እንደሸጠ ፡ በረከትንም ፡ እንዳጣ ፡ እስዚያም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሰጠኋቸውን ፡ ልጅነት ፡ ለእምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ይለውጡታልና ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠንቀቁ ።

ዕብራ ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ፡ ኩፋ ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሐሜት ፡ ትዕቢት ፡ ስድብ ፡ ራስን ፡ መውደድና ፡ ማክበር ፡ መማለጃ ፡ ወይም ፡ ጉቦ ፡ ተቀብሎ ፡



ፍርድ ፡ ማጣመም ፡ ገንዘብ ፡ መቀማት ፡ ወንድምን ፡ መግደል ፡ በሐሰት ፡ መመስከር ፡ መስረቅ ፡ ሐሰት ፡ መናገር ፡ ድንበር ፡ ማፍረስ ፡ ወሰን ፡ መግፋት ፡ አጥር ፡ መስበር፡ቤት ፡ መሰርሠር ፡ ይበዛል፡ወንድምም ፡ ወንድሙን ፡ ለገንዘብ ፡ ይለውጣል ፡ ፍቅርም ፡ ከነሳቸው ፡ ይርቃል ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠበቁ ።

ሄኖክ ፡ ፴፫ ፡ ፲፯ ። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፳፬ ።
ሮ ፡ ፺፬ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻቸው ፡ አይታዘዙም ፡ ባሮችም ፡ ለጌቶቻቸው ፡ አይገዙም ፡ ሴቶች ፡ በመኳንንት ፡ ወንበር ፡ ቢቀመጡ ፡ ይወዳሉ ። በወንድ ፡ መሣሪያ ፡ ያጌጣሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ በዳኝነት ፡ ተቀምጠን ፡ ፍርድ ፡ እንፍረድ ፡ ይላሉ ።

ሴት ፡ የተናገረችው ፡ ለባሏ ፡ አይጥመውም ። ባልዋ ፡ የተናገረውም ፡ ለሚስቱ ፡ አይጥማትም ። የባልዋን ፡ ፈቃድ ፡ አትሠራውም ። ባልዋ ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ይታገሣታል ። ፈቃዱን ፡ ታድርግ ፡ ዘንድ ፡ እሺ ፡ ብትለው ፡ ለጊዜው ፡ ደስ ፡ ይለዋል፡ እምቢ ፡ ብትለውም ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ እያዘነ ፡ ይኖራል ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

ዕዝ ፡ ሉ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሀብታቸውና ፡ ከብልጽግናቸው ፡ የተነሣ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መኖር ፡ ይዘነጋሉ ፡ እህላቸውን ፡ የሚያደልቡበት ፡ ሰፊ ፡ ጐተራ ፡ ለመሥራት ፡ ገንዘባቸውንና ፡ ወርቃቸውን ፡ የሚያከማቹበት ፡ ከፍተኛ ፡ ሣጥን ፡ ለማዘጋጀት ፡



ይፋጠናሉ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የሚበቃሽ ፡ የደለበ ፡ እህል ፡ የተከማቸ ፡ ወርቅና ፡ ገንዘብ ፡ አለሽና ፡ ከእንግዲህ ፡ ዓርፊሽ ፡ ብዪ ፡ ጠጪ ፡ ደስም ፡ ይበልሽ ፡ ይሏታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባላሰቡበት ፡ ሰዓትና ፡ ጊዜ ፡ ሞት ፡ ነፍሳቸውን ፡ ነጥቆ ፡ ይወስዳታል ፡ ያደለቡትና ፡ ያከማቹት ፡ ሀብት ፡ ለማንም ፡ ይሆናል ። እግዚአብሔርን ፡ ያላሰበ ፡ በባለጠግነቱም ፡ ብዛት ፡ የተማመነ ፡ ዕድሉ ፡ እንዲሁ ፡ ይሆናል ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

መዝ ፡ ፵፩ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ።

የሰው ፡ ሕይወት ፡ በገንዘብ ፡ ብዛት ፡ አይጠበቅም ፡ በሀብቱም ፡ መደርጀት ፡ ዕድሜው ፡ አይረዝምም ፡ ከሞትም ፡ አያ

መልጥም ፡ ለሀብት ፡ ከመጉምጀትና ፡ ከከንቱ ፡ ምኞት ፡ ተጠበቁ ።

ሉቃስ ፡ ፲፪—፳፰ ።

ለምትበሉትና ፡ ለምትጠጡት ፡ ወይም ለምትለብሱትና ፡ ለምታጌጡት ፡ አጥብቃችሁ ፡ አትጨነቁ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችን ፡ ተመልከቱ ፡ አይዘሩም ፡ አያጭዱም ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ጐተራ ፡ የላቸውም ፡ ምግባቸውን ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያገኛሉ ። እንዲሁም ፡ አበባዎችን ፡ እዩ ፡ አይደክሙምም ፡ አይፈትሉም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ፡ ጥበበኛውና ፡ እስተዋዩ ፡ ሰሎሞን ፡ ስንኳ ፡ በክብሩ ፡ ሁሉ ፡ ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ አለበሰም ፡ እንግዲህ ፡ ከሰማይ ፡ አሞርችና ፡ ከበረሃ ፡ አበባዎች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ብልጫ ፡ እንዳላችሁ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ እንደተሰጣችሁ ፡ አስቡ ። ከናንተ ፡ መካከል ፡ ተጨንቆና ፡



ተጠቦ ፡ በቁመቱ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ስንዝር ፡ መጨመር ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ እንግዲያውስ ፡ ቲኒሹን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ የማይቻላችሁ ፡ ከሆነ ፡ ስለሌላው ፡ አትጨነቁ

ሉቃስ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫ ።

ከዓመት ፡ ልብሳችሁ ፡ ከዕለት ፡ ጉርሳችሁ ፡ የሚተርፋችሁን ፡ ለነዳያን ፡ መፅውቱ ፡ ከሀብታችሁ ፡ ቀንሣችሁ ፡ ከርስታችሁ ፡ ቆርሳችሁ ፡ ለበጐ ፡ አድራጐት ፡ ስጡ ፡ ከዚያ ፡ ሌባ ፡ በማይሠርቀው ፡ ነቀዝ በማያበላሸው ፡ ብል ፡ በማይበላው ፡ ሰማያዊ መዝገብ ፡ ይከማችላችኋል ፡ ስለዚህም ፡ ተማባር ፡ ወገባችሁ ፡ የታጠቀ ፡ ጆሯችሁ ፡ የነቃ ፡ ዓይናችሁ ፡ የበራ ፡ ይሁን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በማታስቡበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣልና ።

ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ።

ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፪—፴፮ ። ኤፌሶ ፡ ፮ ፡ ፲፩ ።

ወንድማችሁ ፡ ቢበድላችሁ ፡ ለብቻው ፡ ሄዳችሁ ፡ ምከሩት ፡ ምክራችሁን ፡ ቢቀ

በል ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉለት ፡ ባይሰማ ግን ፡ በሁለትና ፡ በሦስት ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ንገሩት ፡ እነርሳቸውንም ፡ ባይሰማ ፡ ለቤተ፡ክርስቲያን፡ንገሯት፡ቤተ፡ክርስቲያንንም፡ባይሰማት፡እንደአረማዊ፡ቍጠሩት ።

ትእዛዙን ፡ ጠብቁ ።

ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭—፲፯ ። ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ፡ ገላ ፡ ፮ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ።

ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡ የምትወዱትን ፡ ሁሉ ፡ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፡ ኦሪትም ፡ ነቢያትም ፡ ይህ፡ ነውና።ለምኑ ፡ ይሰጣችኋል ፡ ፈልጉ ታገኛላችሁ ፡ ደጅ ፡ ምቱ፡ይከፈትላችኋል በጸሎትና፡በእምነት፡የምትለምኑትን፡ሁሉ ትወስዳላችሁ ።

እምነታችሁን ፡ አታጉድሉ ፡

ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ።



ምፅዋታችሁን ፡ ለራሳችሁ ፡ ትታዩና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ትመሰገኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ግብዞች ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እንዳታደርጉ ፡ ተጠንቀቁ ፡ እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ በሰማይ ፡ አባታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ የላችሁም ፡ እናንተስ ፡ ምፅዋት ፡ ባደረጋችሁ ፡ ጊዜ ፡ ቀኝ ፡ እጃችሁ ፡ የሰጠውን ፡ ግራ ፡ እጃችሁ ፡ አይወቅ ። በስውር ፡ የሰጣችሁትን ፡ በስውር ፡ የሚያይ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁ ፡ ዋጋችሁን፡በግልጥ፡ይሰጣችኋል

ትእዛዙን ፡ ጠብቁ ።

ማቴ ፡ ፮ ፡ ፩—፬ ።

በምትጾሙበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ግብዞች ፡ ጾመኛነታችሁን ፡ ለማሳወቅ ፡ ሰውነታችሁን ፡ አታጠውልጉ ፡ ግንባራችሁን ፡ አትቋጥሩ ፡ ፊታችሁን ፡ ታጠቡ ፡ ገጻችሁ ፡ ይብራ ፡ ፈገግታም ፡ ይኑረው ፡ ድካማችሁን ፡ በብርታት ፡ ሠውሩት ፡ በሥውር ፡

የሚያይ ፡ አባታችሁ ፡ ዋጋችሁን ፡ በግልፅ ፡ ይሰጣችኋልና ።

ትእዛዙን ፡ ጠብቁ ።
ማቴ ፡ ፮ ፡ ፲፮—፲፰

እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተዋደዱ ፡ አንድነታችሁን ፡ አጠንክሩ ፡ በመካከላችሁ ፡ መለያየት ፡ አይኑር ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚለያይ ፡ መንግሥት ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠፋል ፡ እርስ ፡ በርሱም ፡ የሚለያይ ፡ ቤት ፡ አደፀናም ፡ ፈጥኖ ፡ ይወድቃል ።

ትእዛዙን ፡ ጠብቁ ።
ዮሐ ፡ ፲፫—፴፬ ፡ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

ወንድሙን ፡ ወይም ፡ ወገኑን ፡ አንት ፡ ጨርቅ ፡ ለባሽ ፡ ድኃ ፡ ብሎ ፡ የሰደበ ፡ በአደባባይ ፡ ይፈርድበታል ። ደንቆሮ ፡ ዲዳ ፡ ዕውር ፡ አንካሳ ፡ ጉባጣ ፡ መላጣ ፡



የሚለው ፡ ግን ፡ በገሃነመ ፡ እሳት ፡ ይፈረድበታል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፩—፳፪ ፡ ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፲፫ ፡ ዘሌዋ ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ፡ ዘዳ ፡ ፲፯ ፡ ፭ ።

እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካልተወለደ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

ትእዛዙን ፡ ጠብቁ ።
ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፭ ፡ ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ፡ ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፭
ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

እኔ ፡ በአብ ፡ እንዳለሁ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ እንዳለ ፡ እመኑ ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ በሥራዬ ፡ እመኑ ። እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ በኔ ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ከእርሱም ፡

የበለጠ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ። መጠራጠር ፡ ወይም ፡ መከራከር ፡ ሳይኖርባችሁ ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የምታህል ፡ ሃይማኖት ፡ ቢኖራችሁ ፡ ተራራውን ፡ ፈልስህ ፡ (ተንሥተህ) ፡ ከባሕር ፡ ግባ ፡ ወርካውን ፡ ካለህበት ፡ ተንቅለህ ፡ ከዚያ ፡ ተተከል ፡ ብትሉት ፡ ትእዛዛችሁን ፡ ይፈጽማሉ ፡ አንዳችም፡የሚሳናችሁ ፡ የለም።

**እምነታችሁን ፡ አታጉድሉ ።**

ማር ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

በከንቱ ፡ አትማሉ ፡ በሰማይ ፡ እንኳ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ነውና ፡ በምድርም ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ (ዱካ) ፡ ናትና ፡ በራሳችሁም ፡ አትማሉ ፡ አንዲቱን ፡ የራስ ፡ ፀጉራችሁን ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቁር ፡ ለማድረግ ፡ አይቻላችሁምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዕውነቱን ፡ ዕውነት ፡ ሐሰ



ቱን ፡ ሐሰት ፡ በማለት ፡ ነገራችሁን ፡ አፅኑ ። ከዚህ ፡ የወጣ ፡ ክፉ ፡ ነውና ።

**ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ።**

ማር ፡ ፭ ፡ ፴ ፡ ፴፯ ። ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ ፡
መዝ ፡ ፵፰ ፡ ፫ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ በመንፈሳቸው ፡ የተቸገሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የርሳቸው ፡ ናትና ።

ማቴ ፡ ፭ ፡ ፫ ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፲፭ ።

ገሮች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱም ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉና ።

መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፲፩ ።

ጽድቅን ፡ የሚራቡ ፡ የሚጸሙም ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይጸግባሉና ።

መዝ ፡ ፵፪ ፡ ፱ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እርሳቸውም ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛሉና ፡

ማቴ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

ልባቸው ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሳቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታልና ፡

ማቴ ፡ ፭ ፡ ፰ ።

ዕርቅ ፡ የሚያደርጉ ፡ እነርሳቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ማቴ ፡ ፭ ፡ ፱ ።

ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚሰደዱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የርሳቸው ፡ ናትና ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲ ።

በሰደቡዋችሁና ፡ በአሳደዱዋችሁም ፡ ጊዜ ፡ ክፉንም ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ በሐሰት በመሰከሩባችሁ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ብፁዓን፡ ናችሁ ። ዋጋችሁ ፡ በሰማይ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡



ነቢያትንም ፡ እንዲሁ ፡ አሳደዋልና ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ሐሤትንም ፡ አድርጉ ።

ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ፡

፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፯ ፡ ፰ ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከልባቸው ፡ ያይደለ ፡ በአፋቸው ፡ ብቻ ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ ይሉኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ የሚሉኝ ፡ ሁሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

ማቴ ፡ ፯ ፡ ፳፩ ።

በምትጸልዩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደግብዞች ፡ በአደባባይ ፡ ቆማችሁ ፡ አትጸልዩ ፡ ነገርም ፡ አታብዙ ፡ እነርሱ ፡ በነገራቸው ፡ ወይም ፡ በጸሎታቸው ፡ መርዘም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰማቸው ፡ ይመስላቸዋ

ሉና ። እናንተስ ፡ በሥውር ፡ እንዲህ ፡ እያላችሁ ፡ ጸልዩ ። በሰማይ ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ስምህ ፡ ይቀደስ፡ መንግሥትህ ፡ ትምጣ ፡ ፈቃድህ ፡ በሰማይ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁ ፡ በምድር ፡ ይሁን ፡ የሚበቃንን ፡ የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ ዛሬ ፡ ስጠን ፡ በደላችንን ፡ ይቅር፡በለን ፡ እኛም ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንል ፡ ዘንድ ፡ የይቅርታ ፡ መንፈስህን ፡ ስጠን ፡ ወደፈተናም ፡ አታግባን ፡ ከክፉ ፡ አድነን፡ እንጂ ፡ መንግሥት ፡ ያንተ ፡ ነውና ፡ ኃይልም ፡ ምስጋናም ፡ ለዘለዓለሙ ።

ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ።
ማቴ ፡ ፮ ፡ ፯ - ፲፭ ።



ክብርንና ፡ ብልጽግናን ፡ ሊበዝትው ፡ የሚወዱ ፡ በፈተና ፡ ይወድቃሉ ፡ በወጥመድም ፡ ይገባሉ ። ለድኃና ፡ ለችጋረኛም ፡ እንዳይሰጡ ፡ እጃቸው ፡ ይታሠራል ። ልባቸው ፡ እንደ ፡ ፈርዖን ፡ ይደነድናል ። የሚድኑበትን ፡ እንዳያውቁ ፡ ዓይናቸው ፡ ይሸፈናል ። ቃሌን ፡ እንዳይሰሙ ፡ ጆሮቻቸው ፡ ይደነቁራል ። እንዳይበሉ ፡ አፋቸው ፡ ይታሰራል ፡ ሆዳቸውም ፡ ይታወካል ። ለማያውቁት ፡ ሰው ፡ ገንዘባቸውን ፡ ያከማቻሉ ። ለልጃቸውም ፡ አያልፍም ። በኃጢአት ፡ እንደ ፡ ተሸፈኑ ፡ ይሞታሉ ።

ንስሐም ፡ አይገቡም ፡

**በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።**
**ዮሐንስ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ።**

ለደጋግ ፡ ማን፡የሚረባ፡የሚጠቅም ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሰጣቸዋል ። ስሜ ፡ ሲነሣ
ይደሰታሉ ። የዚህን ፡ ዓለም ፡ ዋዛ ፡
ፈዛዛ ፡ አይጫወቱም ፡ በሲኦል ፡ ከመጎ
ዛት ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

**ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ፡**

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ጥርስ ፡ አው
ጥተው ፡ ፀጉራቸው ፡ ሸብቶ ፡ ይወለዳሉ ፡
ሃይማኖታቸውን ፡ ያፈርሳሉ ። እንደበታ
ቸው ፡ እንደተሣለ ፡ ምላጭ ፡ ነው ፡ አፋ
ቸው ፡ ለፀመፅና ፡ ለተንኰል ፡ እንደ ፡
ንቃቃት ፡ የተከፈተ ፡ ነው ። ከዕውነት ፡



ይልቅ ፡ ሐሰት ፡ መናገር ፡ ይወዳሉ ፡ ልባ
ቸው ፡ ለክደት ፡ ሆዳቸው ፡ ለከፋት ፡ የተ
ዘጋጀ ፡ ነው ።

**መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፱ ። ዕዝ ፡ ፲ ፡ ፷ ።**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚጣፍጠው ፡ ውሀ ፡
የሚጥመው ፡ እህል ፡ መራራ ፡ ይሆናል ፡
ሕዝብ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ይተላለቃል ።
ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ የሚሠራባት ፡ አገር ፡
ትሠወራለች ፡ ሃይማኖት ፡ የሚጸናባት ፡
አገር ፡ ትጠፋለች ፡ ከቀድሞው ፡ በደል ፡
የበለጠ ፡ በደል ፡ ይሠራል ፡ በአዝርዕት ፡
በአትክልትና ፡ በአበባ ፡ አጊጦ ፡ የሚ
ታየው ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ይፈርሳል ፡ ይጠ
ፋል ፡ መሬት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሆናለች ፡
ዓለም ፡ በመከራ ፡ ትታወካለች ፡ ፀሐይ ፡

በድንገት ፡ ሌሊት ፡ ትወጣለች ፡ ጨረቃም ፡ እንዲሁ ፡ በቀን ፡ ታበራለች ፡፡

**በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ፡፡**
**ዕዝ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡፡ ፮ ፡ ፱ ፡፡**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያንዱ ፡ መንግሥት ፡ ሀገር ፡ የሌላውን ፡ መንግሥት ፡ አገር ፡ በውኑ ፡ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በእውነት ፡ የሚሠራ ፡ አለወይ ፡ ብላ ፡ ትጠይቃለች ፡ እሷም ፡ የለም ፡ ትላለች ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ ከመከራውና ፡ ከስቃዩ ፡ የተነሳ ፡ ሰው ፡ ሞትን ፡ ይመኛል ፡ ከባሕር ፡ ቢጠልቅ ፡ ከገደል ፡ ቢገባ ሞትን ፡ አያገኝም ፡፡

**በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ፡፡**
**ራእይ ፡ ፱ ፡ ፮ ፡፡ ዕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ፡፡**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በየሀገሩ ፡ ሽብር ፡ ይሆናል ፡ እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ተጠቅሎ ፡



ይወርዳል ፡ (የአውሮፕላን ፡ በምብ ?) ከእንጨት ፡ ደም ፡ ይፈሳል ፡ ድንጋይም ፡ አፍ ፡ አውጥታ ፡ ትጮኻለች ፡ (በተአምር) ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወረድሁ ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወለድሁ ፡ የሚል ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ይመጣል ፡ ሕዝብ ፡ ይታወካል ፡ ብዙዎችንም ፡ በምትሐቱ ፡ ያስታል ፡፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንዳያስቱችሁ ፡ በሕግ ፡ ልቡና ፡ ጸንታችሁ ፡ ተቀመጡ ፡፡

**ዕዝ ፡ ፫ ፡ ፩—፱ ፡፡**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ ለብሰው ፡ ከአጋንንት ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ የሚያስቱ ፡ የሚያሳብዱ ፡ የሐሳዊ፡መሢሕን ፡ ነገር ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሰዎች ፡ ይመጣሉ ፡፡ በውስጣቸው ፡ ግን ፡ ነጣቆች ፡ ተኩላዎች ፡ ናቸው ፡፡ በዘመኑ ፡ ትውልድ ፡ ላይ ፡ በማር ፡ የተለወሰ ፡ መርዝ፡ይነዙበታል፡፡ እውነተኛ፡መምህር፡

ለመምሰል ፡ በየአደባባዩ ፡ ሰላምታ ፡ ያበዛሉ ፡ የቆሚሳቸውን ፡ እጅጌ ፡ ያሰፋሉ ፡ የልብሳቸውንም ፡ ዘርፍ ፡ ያስረዝማሉ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ አትመኗቸው ። እምቢ ፡ በሏቸው ። የሚመጣው ፡ የሚታወኩበት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፡ በየለቱ ፡ በየመቱ ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይፈፌመራል ። ሰውም ፡ በምኄሉ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያድርበትም ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠንቀቁ ።
ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ። ፳፫ ፡ ፩—፯ ።
ዘዳግም ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ምሽት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ ፡ ሰማዩ ፡ አትቀልቷል ፡ ብራ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ደመና ሲመጣ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ዝናም ፡ ይዘንማል ፡ እንዲሁም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ነፋስ ፡



በነፋስ ፡ ጊዜ ፡ በሽታ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ የዓየሩንና ፡ የሰማዩን ፡ ጠባይ ፡ ለመመርመር ፡ ይሞክራሉ ። የሰማይን ፡ ሥራ ፡ የዓየርን ፡ ጠባይ ፡ መርምሮ ፡ ማወቅ ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ፡ ሥጋውን ፡ ከነፍሱ ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ለይቶ ፡ መናገር ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ?

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
ሉቃስ ፡ ፲፪ ፡ ፶፬ ፡ ሄኖክ ፡ ፴፭ ፡ ፴፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንት ፡ መሳፍንት ፡ ያገር ፡ ሹማምንት ፡ ከዚያም ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ሠራዊት ፡ በሐሰት ፡ የሚምሉ ፡ በየለቱ ፡ ቃላቸውን ፡ የሚለዋውጡ ፡ ሰዎች ፡ ይፈጠራሉ ። ጢት ፡ የተናገሩት ፡ ለማታ ፡ አይደገምም ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍቅር ፡ የሌላት ፡ ባል
ጀርነት ፡ መተማመን ፡ የሌላት ፡
ጓደኝነት፡ ትፈጠራለች ። ጥል ፡ በደል ፡
መሥራት ፡ መቀማት ፡ ሐሜት ፡ ሐሰት ፡
በልባቸው ፡ የመላ ፡ ሰዎች ፡ ይፈጠራሉ ።
መብል ፡ መጠጥ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሳቸ
ውን ፡ ለገሐነመ ፡ እሳት ፡ ይሸጣሉ ። እና
ንተ ፡ ግን ፡ እንደነሳቸው ፡ አትሁኑ ።

## አጥብቃችሁ ፡ ተጠንቀቁ ።

መዝ ፡ ፪ ፡ ፰ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

በኔ ፡ ፈቃድ ፡ ለሚሔዱ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡
በቅን ፡ ልቡና ፡ በሌሊትና ፡ በመዓልት ፡
ለሚገዙልኝ ፡ ሰዎች ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ወዳ
ጆቼ ፡ እንደ ፡ አብርሃምና ፡ ይስሐቅ ፡
እንደ ፡ ያዕቆብና ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ባሮቼ ፡



እንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ዳንኤል ፡ እንደ ፡
ኤልያስና ፡ እንደ ፡ ሚክያስ ፡ በሚመጣው
ዘመን ፡ እጠብቃቸዋለሁ ። ተድላ ፡ መን
ግሥት ፡ ሰማያትንም ፡ አወርሳቸዋለሁ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወሬ ፡ ለመስማት ፡
ነገር ፡ ለማየት ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ይቅ
በዘበዛሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያዩትንና ፡ የሰ
ሙትን ፡ በልቡናቸው ፡ አያሳድሩም ።

## በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠበቁ ።

ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፳ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚያ
ቃጥሉ ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡
ይፈጠራሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክረምትና ፡
በጋ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይሆናሉ ። ዝናምም ፡
ካመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ይዘንማል ፡ የእ

ሀል ፡ በረከትም ፡ ይጐድላል ። የሰውም ፡ ኃይል ፡ ሲሶ ፡ ይቀንሣል ። የበቅሎ ፡ የግመል ፡ የእንስሳ ፡ የአራዊት ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ ይነሳለታል ፡ ቅቤም ፡ ማርም ፡ ጣዕም ፡ በረከትም ፡ የለውም ። በዓመት ፡ በዓመቱ ፡ እየተቀነሰ ፡ ይሔዳል ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠበቁ ።

ወርቅ ፡ ይናቃል ፡ መዳብ ፡ ይከብራል ። ወርቅ ፡ የተባለው ፡ ወርቅ ፡ አይደለም ፡ ወርቅ ፡ የተባሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ። መዳብ ፡ የተባሉ ፡ አረመኔዎች ፡ ናቸው ። አረመኔዎች ፡ ራሳቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋሉ ። ግብዞችና ፡ ማስተዋል ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ እለዚያን ፡ ይወዳሉ ። ያከብሯቸዋልም ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተጠበቁ ።
ዘዳግም ፡ ፳፰ ፡ ፵፫—፵፬



በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ለሰባት ፡ ሴቶች ፡ ባል ፡ ይሆናል ፡ እነሱም ፡ እንጀራችንን ፡ ሠርተን ፡ እንበላለን ፡ ልብሳችንንም ፡ ፈትለን ፡ እንለብሳለን ፡ ስምህ ፡ ብቻ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ በባልነት ፡ ይጠራ ፡ ባል ፡ የላቸውም ፡ ከመባል ፡ አድነን ፡ ይላሉ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
ኢሳ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በናታቸው ፡ ማኅፀን ፡ ሣሉ ፡ የሚጮሁ ፡ ውሾች ፡ ይወለዳሉ ፡ ውሾች ፡ የተባሉት ፡ ውሾች ፡ አይደሉም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ናቸው ፡ እንጂ ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የሚወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ቃላቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋሉ ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ይነሣሣሉ ፡ ለወላጆቻቸው ፡ አይታዘዙም ፡

አባት ፡ እናታቸውን ፡ አያከብሩም ፡ እናንት ፡ የመናገር ፡ ችሎታ ፡ የላችሁም ፡ እኛ ፡ እንናገር ፡ ነገራችንን ፡ አታስናክሉብን ፡ ይሏችዋል ፡ ሞትን ፡ አያስቡም ፡ አሊህም ፡ አእምሮ ፡ የጐደላቸው ፡ መንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተለያቸው ፡ ናቸው ።

እግዚአብሔር ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ስለ ታገሣቸው ፡ እንደሌለ ፡ ይቆጥሩታል ፡ በሥራቸው ፡ የጐሰቆሉ ፡ በሀሳባቸው ፡ የረከሱ ፡ ናቸው ። ባሕላቸውን ፡ ይለውጣሉ ። የያዙትን ፡ ይጥላሉ ። ያላዩትን ፡ ይናፍቃሉ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕሪያቸውን ፡ በእንስሳ ፡ ባሕርይ ፡ ይለውጣሉ ፡ ነውርን ፡ ይንቃሉ ፡ ኃፍረታቸውን ፡ ይገልጣሉ ፡ ሥጋዊ ፡ ፍትወትን ፡ በሚያስፈ



ጽሙ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ የሐሳዊ ፡ መሲሖች ፡ ተንኰል ፡ ልባቸውን ፡ ያጠፉዋል ፡ አምላካቸውን ፡ ያስረሳቸዋል ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ የወገን ፡ ክብር ፡ አይሰማቸውም ፡ የአባት ፡ እናታቸውን ፡ ምክር ፡ አይቀበሉም ፡ ተዉን ፡ ልቀቁን ፡ እንሩጥ ፡ እንፈርጥጥ ፡ ይላሉ ።

በዝሙት፡ፍቅር፡ይነደዳሉ ። በየሸለቆውና በየጐጡ፡እንደበግ ፡ ታግተው ፡ ሬሬሳማ ፡ ለብሰው ፡ የሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፡ ከሰዶምና ፡ ከገሞራ ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ ያልተለየ፡ነው ፡ የሚያደርጉትን ፡ አያውቁትም እግዚአብሔር ፡ አያስተውልም ፡ ይላሉ ፡ ይመለከታቸውም፡አይመስላቸውም፡እሱ፡ግን፡ከሰማይ ፡ ሆኖ፡ ይሳለቅባቸዋል ። ይስቅባቸዋልም ። በመዓቱም፡ ያውካቸዋል ። በውኑ፡ጆሮን፡የሠራ፡እግዚአብሔር፡ አይሰ

ማምን ፡ ዓይንንስ ፡ የፈጠረ ፡ እምላክ ፡ አያይምን ፡ በዚህም ፡ ግብራቸው ፡ ዕድሜ ያቸው ፡ ያጥራል ፡ በወጣትነት ፡ ዘመና ቸው ፡ ይቀሠፋሉ ፡ ፈጥነውም ፡ ይጠፋሉ

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
መዝ ፡ ፲፫ ፡ ፩—፪ ። ፪ ፡ ፬ ። ማቴ ፡ ፲፪ ፡
ሄኖክ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ፡ መዝ ፡ ፶፫ ፡ ፱ ።
ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ። ዘዳግም ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለብዙ ፡ ክብር ፡ የታጩ በማዕርግ ፡ በሹመት ፡ ያደጉ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሁሉ ፡ አደራቸ ውን ፡ ይዘነጋሉ ፡ ሀገራቸውን ፡ ይከዳሉ ፡ መሐላቸውን ፡ ያፈርሳሉ ፡ ከባለሟልነታ ቸው ፡ ይወጣሉ ፡ ከማዕርግና ፡ ሹመት ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ይለያሉ ። ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ በተገለጸባቸው ፡ ጊዜ ፡ ማን ፡ ይፀፀታሉ ፡



በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ታንቀው ፡ ተሰቅለው ፡ ወይም ፡ በአልባሌ ፡ ቦታ ፡ ወድቀው ፡ ይሞታሉ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
ማቴ፡ ፳፯፡ ፫—፰ ። የሐ፡ሥራ፡ ፩—፲፯ ።

አባት ፡ ልጁን ፡ ወንድምም ፡ ወንድ ሙን ፡ ይጠላል ፤ እኅት ፡ እኅቷን ፡ እማ ትም ፡ ምራቷን ፡ አትወድም ፤ ባልንጀ ራም ፡ ባልንጀራውን ፡ ይከዳል ።

አባትም ፡ ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡ ልጆቻቸውም ፡ አባት ፡ እና ታቸውን ፡ ያስገድሏቸዋል ። ለሰው ፡ ጠላቱ ፡ ቤት ፡ ሰቡ ፡ ይሆናል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
ማርቆስ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፮ ።

አበያና ፡ ባለሙያ ፡ በሬዎች ፡ ይጠመዳሉ ፡ የሚስበውን ፡ ይገርፉታል ፡ አበያውን ፡ ይተዉታል ። በሬ ፡ የተባለ ፡ በሬ ፡ አይደለም ። ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዋስ ፡ ይከፍላል ፡ ባለዕዳ ፡ ያመልጣል ። የሚይዘውም ፡ የለም ።

**በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።**

**ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴ ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፴፯ ።**

ብሉን ፡ ብሉን ፡ የሚሉ ፡ ጣፋጭ ፡ ፍሬዎች ፡ ወይንና ፡ ትርንጎ ፡ ይፈጠራሉ ፡ ይናቃሉ ፡ እንጂ ፡ የሚበላቸው ፡ የለም ፡ ዕሬት ፡ መራራ ፡ ይባላሉ ፡ ወይንና ፡ ትርንጎ ፡ የተባሉት ፡ ወይንና ፡ ትርንጎ ፡ አይደሉም ፡ መጻሕፍትና ፡ ሊቃውንት ፡ መምህራን ፡ ናቸው ፡ ሲመክሩ ፡ ሲያስተ



ምሩ ፡ ይንቋቸዋል ፡ እንጂ ፡ አይሰሟቸውም ።

**በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።**

**ሄኖክ ፡ ፴፮ ፡ ፴ ።**

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬዎች ፡ በታቸውን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ይገባሉ ፡ አውሬ ፡ የተባሉ ፡ ባሕታውያን ፡ ናቸው ፡ ባሕታውያን ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ የብሕትውናን ፡ ሥራ ፡ አይሠሩም ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ሌሊት ፡ መንቃት ፡ የለባቸውም ። መነኰሳት ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ አይሠሩም ። ፈቃደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አይፈጽሙም ፡ ወንድማቸውን ፡ ባልንጀራቸውን ፡ አይወዱም ፡ እንደ ፡ ዓለማዊ ፡ ሰው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ሹመት ፡ ይሻሉ ።

በረከቱን ፡ ቸርነቱን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ሳፈስ ፡ ይህንን ፡ ትተው ፡ መራራ ፡ ይበ
ላሉ ። የማር ፡ ዘፈን ፡ ይወዳሉ ። በዚያን ፡
ዘመን ፡ ሠራዊቱም ፡ መኳንንቱም ፡ ነገሥ
ታቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ደንቆሮውም ፡ ብል
ሁም ፡ ንጹሑም ፡ ርኩሱም ፡ ባሪያም ፡
ጌታም ፡ ለኢጋንንት ፡ ያድራሉ ። በኃጢ
አት ፡ በትእቢት ፡ ይታጀራሉ ፡ ፍቅር ፡
ትሕትና ፡ ስለሌላቸው ፡ ጸሎታቸው ፡
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡
ዕጣናቸውም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አያርግም ።
እነዚህን ፡ ለመሳሰሉ ፡ ሁሉ ፡ የገነት ፡
ደጅ ፡ አይከፈትላቸውም ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

ቁራ ፡ ቀሚስ ፡ ወዳንገቱ ፡ ያጠልቃል ።
ቁራ ፡ የተባለ ፡ ቁራ ፡ አይደለም ። ቄስ ፡



ናን ፡ የሚሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ያላደረባቸው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
የማይሔዱ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚወዱ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ትተው ፡
የዚህን ፡ ዓለም ፡ የተከተሉ ፡ ሕጉን ፡
ትተው ፡ ሦስት ፡ አራት ፡ ሚስት ፡ የሚያ
ገቡ ፡ ለወንዱም ፡ ለሴቱም ፡ ሐሰት ፡ የሚ
ያስተምሩ ፡ በስሜ ፡ የሚገዙትን ፡ ለአም
ልኮቱ ፡ የሚቀኑትን ፡ የማንቁ ፡ ናቸው ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደንቆሮች ፡ ብልሆች ፡
ብልሆችም ፡ ደንቆሮዎች ፡ ይሆናሉ ።

ውሃ ፡ አሻቅቦ ፡ ይፈሳል ። ውሃ ፡ አሻ
ቅቦ ፡ ይፈሳል ፡ የተባለው ፡ በማይገባቸው
እኔ ፡ እንግሥ ፡ እኔ ፡ እንግሥ ፡ የሚሉ ፡
ናቸው ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡

ንጉሥ ፡ ሳለሁ ፡ የምነግድል ፡ የማድን ፡ የምቀጣ ፡ የምምር ፡ የምሾም ፡ የምሽር ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ከእኔ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለምና ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

ዘሙሴ ፡ ፲ ፡ ፲፰ ፡ ፴፱ ። ኢሳ ፡ ፳፯ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ፲፫ ። ዘዐ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፫ ።

በዚያን ፡ ወራትና ፡ ዘመናት ፡

እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ የሚፈረድባት ፡ ከተማ ፡ ፍርድ ፡ ይጣመምባታል ፡ ጽድቅ ፡ ሰፍኖባት ፡ የነበረች ፡ አገር ፡ የነፍስ ፡ ገዳዮችና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወንጀለኞች ፡ ዋሻ ፡ ትሆናለች ። ባለሥልጣኖችና ፡ ሹማምንቶች ፡ ከእመጻኞች ፡ ጋራ ፡ ይተባበራሉ ፡ ሁሉም ፡ ጉቦ ፡ ይወዳሉ ፡ መማለጃ ፡ ይቀበላሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እጅ ፡ መንሻንም ፡ ለማግኘት ፡ ይጣደፋሉ ፡ በዚህም ፡ የተ



ነሣ ፡ በደሀና ፡ በሀብታም ፡ መካከል ፡ ትክክል ፡ አይፈርዱም ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፭ ።

ስለጉቦና ፡ ስለመማለጃ ፡ ሐሰተኛውን ፡ እውነተኛ ፤ እውነተኛውን ፡ ሐሰተኛ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ክፉውንም ፡ መልካም ፡ መልካሙንም ፡ ክፉ ፡ ለሚሉ ፡ ጨለማውን ፡ ብርሃን ፤ ብርሃኑን ፡ ጨለማ ፡ ለሚያደርጉ ፡ መራራውን ፡ ጣፋጭ ፡ ጣፋጩን ፡ መራራ ፡ ለሚሉ ፡ ወዮላቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

ስለዚህ ፡ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ቃርሚያን ፡ እንዲበላ ፡ አበቅም ፡ (ገለባም) ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ እንደሚጠፋ ፡ አመድም ፡

በነፋስ ፡ ኃይል ፡ ተጠርጎ ፡ እንደሚበን ፡
እንዲሁ ፡ የነሱ ፡ ሥር ፡ ይበሰብሳል ፡ ቡቃ
ያውም ፡ ይደርቃል ፡ እንደትቢያም ፡ ይበ
ናል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ተላልፈ
ዋልና ፡ የተናገረውንም ፡ ቃሉን ፡ አቃ
ለዋልና ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

## ኢሳ ፡ ፳ ፡ ፰ ።

ሰብል ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንበጣ ፡
ኩብኩቤ ፡ የምድራቸውን ፡ ፍሬ ፡ የሚ
በላ ፡ መቅሰፍት ፡ ይላክባቸዋል ፡ በያገሩ ፡
ጸብ ፡ ክርክር ፡ ይነሣል ። ነጋድያን ፡ ወዲ
ያና ፡ ወዲህ ፡ ብለው ፡ እንዳይነግዱ ፡ የባ
ሕር ፡ ወደብ ፡ (ካናል) ፡ ይዘጋባቸዋል ።
ልብስ ፡ ይታጣል ። ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ቢሰጡ ፡
አይገኝም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንብረት ፡ የተ



በላሸ ፡ ነው ። በጉም ፡ ላሙም ፡ እንስሳ ፡
ሁሉ ፡ ያልቃል ። ቤቱ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዘ
ጋል ። ዕጣንም ፡ አይገኝ ። የሚፈጃቸው ፡
ዘንዶ ፡ ይመጣል ፡ ተኩላም ፡ አባብም ፡
ጅብም ፡ ነምርም ፡ አንበሳም ፡ ይፈጃቸ
ዋል ። የሮጠ ፡ አያመልጥም ፡ የተሠማ
ራም ፡ ተመልሶ ፡ አይገባም ። የዶሮን ፡
ጫጩት ፡ ከእናታቸው ፡ ብብቻ ፡ እየነ
ጠቀ ፡ እንደሚወስድ ፡ ጠላፊ ፡ አሞራ ፡
ይላክባቸዋል ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ረኀብ ፡ ችጋር ፡ ይሆ
ናል ። ሰው ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፡ ብዙ
ዎችም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሣር ፡
ይግጣሉ ። ሀገርም ፡ ይጠፋል ። ሥጋዬን ፡
ደሜን ፡ ያረክሳሉ ። ምሥጢሬን ፡ ለሁሉ ፡

ይገልጣሉ ። ከወዳጆቻቸውና ፡ ከዘመዶቻ ቸው ፡ ጋራ ፡ ይሊስናሉ ። ስሙኑታቸውን ፡ ያሳድፉሉ ፡ ባልፈጠራቸው ፡ ያመልካሉ ። ስለዚህ ፡ የሚፈጁቸው ፡ ጨካኝ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሥባቸዋል ፡ ታላቁም ፡ ታናሹም ፡ ያልቃሉ ። ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ መነኰሳትም ፡ ካህናትም ፡ ሕዝብም ፡ በየገሩ ፡ ሁሉም ፡ ያልቃል ። እለዚያውም ፡ ከዚህ ፡ ከመከራ ፡ የተረፉት ፡ ስንኳ ፡ ልባቸው ፡ አይመለስም ። በልቡናቸው ፡ ድንቁርና ፡ መልቷልና ። እኔም ፡ ቁጣዬን ፡ ከሳቸው ፡ አላበርድም ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠበቁ ።

የእሕዛብ ፡ ቀን ፡ እንደደረሰ ፡ ዕወቁ ። ለእሕዛብ ፡ በሩቅ ፡ ምልክት ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ በፋጤት ፡



ይጠራሉ ፡ እነሱም ፡ እየተጣደፉ ፡ ፈጥነው ፡ ይመጣሉ ፡ ደካማና ፡ ሰንኩል ፡ የለባቸውም ፡ የሚያንቀላፋና ፡ የሚተኛ ፡ የለም ፡ የወገባቸው ፡ ትጥቅ ፡ አይፈታም ፡ የጫማቸው ፡ ማሰሪያ ፡ አይበጠስም ፡ እንደአንበሳ ፡ ያገሳሉ ፡ እንደባሕር ፡ መትመም ፡ ይተማሉ ፡ የጥፋት ፡ ክንዳቸውን ፡ ያነሳሉ ፡ እጃቸውንም ፡ ለምርኮ ፡ ይዘረጋሉ ፡ የሚያድንም ፡ የለም ፡ ብርሃን ፡ ትሠወራለች ፡ ምድርም ፡ ትጨልማለች ፡ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ብዙ ፡ ጭንቅና ፡ መከራም ፡ ይሆናል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፮ ። ዕዝ ፡ ፭ ፡ ፫ ።

በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ጎግ ፡ ከሰሜን ፡ ዳርቻ ፡ ይወጣል ፡ የሠራዊቱ ፡ ብዛት ፡

ምድርን ፡ እንደጉም ፡ ይሸፍናል ፡ ሠራ
ዊቱን ፡ እየመራ ፡ በእሥራኤል ፡ ላይ ፡
በዘመተ ፡ ጊዜ ፡ መቅሰፍትና ፡ መዓት ፡
ይወርዳል ፡ መሬትም ፡ ትንቀጠቀጣለች ፡
ከጽኑ ፡ መንቀጥቀጥ፡የተነሣ ፡ የባሕር ፡ ዓሣ
ዎችና ፡ የሰማይ ፡ አእዋፎች ፡ በምድረ ፡
በዳ ፡ ያሉ ፡ አራዊቶች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎችና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ፍጥረ
ቶች ፡ ሁሉ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፡ ተራሮች ፡
ይገለባበጣሉ ፡ ገደሎች ፡ ይናዳሉ ፡ አጥ
ርና ፡ ቅጥሮች ፡ ይፈራርሳሉ ፡ ታላቅ ፡
ጦርነት ፡ ይሆናል ፡ በሞስህና ፡ በቶቤል ፡
አለቃ ፡ በጎግ ፡ ላይ ፡ ዶፍና ፡ የበረዶ ፡
ድንጋይ ፡ እሳትና ፡ ድኝም ፡ በእርሱና ፡
በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ ይዘንማል ። በእጁ ፡
የጨበጠውን ፡ በጫንቃው ፡ የተሸከመው
ንና ፡ በወገቡ ፡ የታጠቀውን ፡ ልዩ ፡ መሣ



ሪያ ፡ ይጥላል ፡ እሱና ፡ ሠራዊቱ ፡ ከሱም ፡
ጋር ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ በእሥራኤል ፡
ተራሮች ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፡ ሥጋቸውም
ለሰማይ ፡ አሞሮችና ፡ ለምድር ፡ አራዊ
ቶች ፡ መብል ፡ ሆኖ ፡ ይሰጣል ፡ በእሥ
ራኤል ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ የጎግን ፡
የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለመማረክ ፡ ይወጣሉ ፡
ታንኩንና ፡ መድፉን ፡ ሌላውንም ፡ ከባ
ድና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡
በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ፡ ከጦር ፡ መሣሪያው ፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ለቤት ፡
ማገዶ ፡ ያደርጉታል ፡ ከዱር ፡ እንጨት ፡
አይለቅሙም ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።
## ሕዝ ፡ ፴፰ ፡ ፲፮ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በእሥራኤል ፡ ባሕር ፡
በስተምሥራቅ ፡ ያሉ ፡ ሸለቆዎች ፡ ለጎ

ማና ፡ ለሠራዊቱ ፡ መቃብር ፡ ይሆናሉ ፡ ከራማውና ፡ ከመቃብሩ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ መተላለፊያ ፡ አይገኝም ፡ መንገድን ፡ ይዘጋል ፡ የጎግን ፡ ሠራዊት ፡ ለመቅበርና ፡ ምድሯንም ፡ ለማጽዳት ፡ የእሥራኤልን ፡ ሕዝብ ፡ ሰባት ፡ ወር ፡ ይፈጅባቸዋል ፡ መቃብር ፡ ለመቆፈርና ፡ ሬሳውን ፡ ለመቅበር ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ ይቀጠራሉ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ከመቃብር ፡ የቀረውን ፡ ከሰማይ ፡ አሞራና ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ የተረፈውን ፡ በመቆጣጠር ፡ ምድራቱን ፡ እየዞሩ ፡ ያጸዳሉ ።

## በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተጠንቀቁ ።

## ሕዝ ፡ ፴፱ ፡ ፲፩ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መሬት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ትንቀጠቀጣለች ። በደቡብ ፡



በኩል ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ይነሣል ። ቤታቸውን ፡ ያፈርሳል ። ሰውም ፡ ያልቃል ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ብርቱ ፡ (ጎርፍ) ፡ ዝናም ፡ ብርቱ ፡ ክረምት ፡ ይመጣል ። ፀሐይንም ፡ ጉም ፡ ይሸፍናታል ። ፯ ፡ ቀን ፡ ትጨልማለች ። ብርሃኗ ፡ ይደክማል ። መብረቅ ፡ ነጎድጓድ ፡ ይመጣል ። ምድርም ፡ ትጠፋለች ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አደረግሁ ፡ ጌታዬ ፡ ትለኛለች ። እኔም ፡ ባንቺ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እኔን ፡ አላወቀምና ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ ማድረጌ ፡ እንዲያውቁት ፡ ነበር ፡ አላታለሁ ። የምድር ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡ በብዙ ፡ ድርቅ ፡ ይጠፋሉ ። ደግሞ ፡ በክንፉ ፡ የሚሰበስብ ፡ አሞራ ፡ እልካለሁ ። እሱም ፡ ፳፬፻፵፯ ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ የሚገድል ፡ ነው ። ከነዚያውም ፡

የተዘጋጀ ፡ የለም ። በግና ፡ ፍየል ፡ ያልኋ
ቸው ፡ ጻድቃንና ፡ ኃጥአን ፡ ናቸው ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡
መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ይሰበሰባሉ ፡ በመከራ ፡
ይተሳለቃሉ ። ሥጋዬን ፡ ደሜን ፡ ያረከሱ ፡
በሐሰት ፡ በስሜ ፡ የማሉ ፡ ፈቃዴን ፡ ያል
ፈጸሙ ፡ በጽኑዕ ፡ አሠራቸዋለሁ ። በዚ
ያው ፡ ዘመን ፡ ሞትን ፡ አስናብተዋለሁ ።
ሸሽተውም ፡ አያመልጡም ፡ የሚያድና
ቸውም ፡ የለም ። ፈርዖን ፡ ከነሠራዊቱ ፡
እንደሰጠመ ፡ ይሆናሉ ። ፲፯ ፡ ቀን ፡ ይዋ
ጋሉ ። በከፋታቸው ፡ ያልቃሉ ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ የተጠ
በቁ ፡ የጾሙ ፡ የጸለዩ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡
ይተርፋሉ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምድር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡
ብቻዋን ፡ ትቀራለች ፡ አይጥና ፡ ፍልፈል ፡ ይሰ



ለጥናሉ ። ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፉሉ ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ከምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ታሪካዊና ፡
ደገኛ ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ፡ እሱም ፡ ፈቃ
ዶን ፡ የፈጸሙትን ፡ ከመከራ ፡ ያተረፍኋ
ቸውን ፡ የሚሰበስብ ፡ ነው ። ጳጳስም ፡
ይወጣል ። ምድርን ፡ የሚባርክ ፡ ሰውን ፡
ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። አብያተ ፡ ክርስቲ
ያናት ፡ ይታደሳሉ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ መቅ
ሠፍት ፡ የለም ። ምሕረት ፡ በረከት ፡ ይበ
ዛል ። ያለ ፡ ደመና ፡ ሰምንት ፡ ቀን ፡ ይዘን
ማል ። ይህም ፡ ዝናም ፡ በረከት ፡ ፍቅር ፡
ነው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተኩላ ፡ ከበግ ፡ አውራ ፡
ጋር ፡ ይጫወታል ፡ ነብርም ፡ ከፍየል ፡
ጠቦት ፡ ጋር ፡ ይተኛል ፡ አንበሳና ፡ ላም ፡
አብረው ፡ ይሠማራሉ ፡ እህያና ፡ ጅብ ፡
አንድነት ፡ ይውላሉ ። ግልገሎቻቸውም ፡

የምግብ ፡ ዓይነት ፡ ሁሉ ፡ ሞልቷል ፡ ተር
ፈል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሳታይ ፡ ሄደሃልና ፡ ተነሥ
ተህ ፡ እይ ፡ ይለዋል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የአ
ንድ ፡ በሬ ፡ እሸት ፡ የአንዲት ፡ ላም ፡
ወተት ፡ ለብዙ ፡ ይበቃል ። ፍቅር ፡
ሰላም ፡ ደስታና ፡ ተድላ ፡ እንጂ ፡ ፀብ ፡
ክርክር ፡ ጦርነት ፡ የለም ። ሰውም ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ በቅንነትና ፡ በበጎ ፡ መንፈስ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ይገዛል ።

ሄኖክ ፡ ፫ ፡ ፳—፳፩ ። መዝ ፡ ፺፫ ፡ ፴ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በ፫ ፡ ወገን ፡ ፫ ፡ ነገሥ
ታት ፡ ይነግሣሉ ። አንዱ ፡ ወደ ፡ ምሥ
ራቅ ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አንዱ ፡
ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይሄዳሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ይመጣል ። እኔ ፡ ክርስ



ቶስ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያስ
ታል ። በያገሩ ፡ መከራ ፡ ይወርዳል ።
ሰማይ ፡ ምድር ፡ ያልፉል ። ፀሐይ ፡
ጨረቃ ፡ ከዋክብትም ፡ ሁሉ ፡ ይጠፉሉ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከቅዱሳን ፡ መላ
እክቱ ፡ ጋራ ፡ በግርማ ፡ መንግሥቱ ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በጌትነቱ ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ።

ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፱ ፡ ፴፫ ።

ዳግመኛም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የመለከት ፡
መነፋት ፡ ይሆናል ፡ ይኸውም ፡ ሙታንን ፡
የሚያነቃ ፡ ነው ።

በመጀመሪያው ፡ አዋጅ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡
ዳርቻ ፡ የተበተኑን ፡ የሥጋ ፡ ትቢያ ፡ ይሰበ
ሰባል ፡ በላይ ፡ ያለውና ፡ በታች ፡ ያለው ፡
በባሕርና ፡ በየብስ ፡ ያለው ፡ አውሬ ፡

የበላው ፡ ገደል ፡ የገባው ፡ ውሀ ፡ የወሰደው ፡ እንዲሁም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞት ፡ ፈጽሞ ፡ ያረጀና ፡ የጠፋ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ የሥጋ ፡ ቅርፍት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ቀደመ ፡ መገናኛው ፡ ይሰበሰባል ።

በሁለተኛው ፡ አዋጅ ፡ አጥንቶች ፡ ከሥጋና ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ ይያያዛሉ ፡ ያለ መንቀሳቀስ ፡ ያለመናወጥም ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፡ ፍጹም ፡ በድን ፡ ይሆናሉ

በሦስተኛው ፡ አዋጅ ፡ ሙታን ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ ይነሣሉ ፤ ጻድቃንና ፡ ኃጥአን ፡ ክፉም ፡ ቢሆን ፡ ደግም ፡ ቢሆን ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከምድር ፡ የተከተላቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ተሸክመው ፡ ይነሣሉ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በቀኝ ፡ የቆሙትን ፡ እናንተ ፡ የአባቴ ፡ ቡሩካን ፡ ዓለም ፡ ሣይ



ፈጠር ፡ ያዘጋጀሁላችሁን ፡ መንግሥት ፡ ስማያትን ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወዶኔ ፡ ኑ ፡ ይላቸዋል ።

ብራብ ፡ አብልታችሁኛልና ። ብጠማ ፡ አጠጥታችሁኛልና ። እንግዳ ፡ ብሆን ፡ አሳድራችሁኛልና ። ብታረዝ ፡ አልብሳችሁኛልና ። ብታመም ፡ ጐብኝታችሁኛልና ።

ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩—፵፮ ።

በጐችን ፡ በቀኙ ፡ ፍየሎችንም ፡ በግራው ፡ ያቆማል ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ የተባሉ ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ አይደሉም ፡ ጻድቃንና ፡ ኃጥአን ፡ ናቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይመልሱለታል ፤ አቤቱ ፡ መቼ ፡ ተርበህ ፡ አይተን ፡ አበላንህ ፡ ወይስ ፡

ተጠምተህ ፡ አጠጣንህ ። መቼስ ፡ እንግዳ ፡ ሆነህ ፡ አይተን ፡ ተቀበልንህ ፡ ወይስ ፡ ታርዘህ ፡ አለበስንህ ። መቼ ፡ ታመምክና ፡ አየንህ ፡ ወይስ ፡ መቼ ፡ ታሥረህ ፡ ጠየቅንህ ።

ንጉሡም ፡ መልሶ ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሽ ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ ያደረጋችሁት ፡ ለእኔ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ነው ፡ ይላቸዋል ።

ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፩—፵ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በግራ ፡ የቆሙትን ፡ እናንተ ፡ ርጉማን ፡ ከእኔ ፡ ወግዱ ፡ ለሰይጣንና ፡ ለሠራዊቱ ፡ ወደ ተዘጋጀ ፡ ወደዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ሂዱ ። ብራብ ፡ አላበላችሁኝምና ። ብጠማ ፡ አላጠጣችሁኝምና ። እንግዳ ፡ ብሆን ፡ አላሳደራችሁኝምና ።



ብራቆት ፡ አላለበሳችሁኝምና ። ብታመም አልጎበኛችሁኝምና ። ብታሠር ፡ አልጠየቃችሁኝምና ፡ ይላቸዋል ።

ማቴዎስ ፡ ፳፭ ፡ ፵፬ ያዕቆብ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።

እነርሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ አቤቱ ፡ ተርበህ ወይስ ፡ ተጠምተህ ፡ ወይስ ፡ እንግዳ ፡ ሆነህ ፡ ታርዘህ ፡ ወይስ ፡ ታመሕና ፡ ታሥረህ ፡ መቼ ፡ ዐይተንህ ፡ አልጠየቅንህም ይሉታል ፡ ንጉሡም ፡ እውነት ፡ እውነት እላችኋለሁ ፡ ከዚህ ፡ ከታናናሾች ፡ ላንዱ ያላደረጋችሁት ፡ ለኔ ፡ አላደረጋችሁም ፡ ብሎ ፡ ይመልስላቸዋል ።

ማቴዎስ ፡ ፳፭ ፡ ፵፮ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ዓመፅንና ፡ ተንኮልን ፡ ይናገር ፡ የነበረ ፡ አፍና ፡ አንደበት ፡ ሁሉ ፡ ይዘጋል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ኀዘን ፡ ይደረጋል ፡ የማይጠቅም ፡ ኀዘን ፡ ነው ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ጨኸት ፡ ይሆናል ፡ የማይ
ጠቅም ፡ ጨኸት ፡ ነው ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡
ፍጅት ፡ ይሆናል ፡ የማይጠቅም ፡ ፍጅት ፡
ነው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ልቅሶ ፡ ይሆናል ፡ የማ
ይጠቅም ፡ ልቅሶ ፡ ነው፤እናት፡የልጅዋን ፡
ልቅሶና ፡ ጨኸት ፡ አትሰማም ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ ፍጻሜ ፡ ማኅለቅት ፡ እንደሌለው ፡
እንደክረምት ፡ ውሀ ፡ ዕንባ ፡ ይፈሳል ፤
ነጣቂ ፡ መብረቅ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ የነጐ
ድጓድ ፡ ቃልም ፡ የሚቆርጥና ፡ የሚከፋ
ፍል ፡ የሚለይ ፡ ብርቱ ፡ ብልጭልጭታም
ይላካል ። ይኸውም ፡ የኃጥአን ፡ ዕድል ፡
ፈንታቸው ፡ ነው ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ አደራዋን ፡ ትመል
ሳለች ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በሕይወትዋ ፡ዘመን
የሠራችው ፡ የነፍስ ፡ ሥራዋ ፡ ይገለጻል ።



ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ይሰበሰ
ባል ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ አንዲት ፡
ቀን ፡ ይሆናል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡
ከኃጥአን ፤ ኃጥአን ፡ ከጻድቃን ፡ ይለያሉ ።
ርኵሳንም ፡ ከንጹሓን ፡ ይለያሉ ። ሥራቸው
ክፉ ፡ የሆነ ፤ ነገሥታት ፤ መኳንንት ፤ ሰነ
ፎች ፡ ቀማኞች ፡ ካህናት ፡ መነኰሳት ።
ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚናገሩ ፡ ባንደ
በታቸው ፡ ሐሜት ፡ የሚአበዙ ፡ ምግባራ
ቸው ፡ ይገለጻል ። በኔ ፡ ፊት ፡ ያፍራሉ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ ያዘኑ ፡ ደስ ፡ ይላ
ቸዋል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ያበዙ ፡
ያዝናሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በስሚ ፡ መከራ ፡
የተቀበሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እኔን ፡ ያላ
መኑ ፡ ከሐዲዎች ፡ ያዝናሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡
ትሕትና ፡ የሠሩ ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡

ይከብራሉ ። ትዕቢትን ፡ ያበዙ ፡ ግን ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ይወርዳሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በስሜ ፡ የሞቱ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ያገኛሉ ። ወዳጆቼን ፡ ጻድቃንን ፡ የገደሉ ፡ ግን ፡ ያፍራሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በስሜ ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ ፊታቸው ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ያበራል ። ወዳጆቼን ፣ ባሮቼን ፣ በመከራ ፡ የጣሉ ፡ ከመከራ ፡ ይወድቃሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በስሜ ፡ የተራቡ ፡ ይጠግባሉ ። ዓለምን ፡ የናቁ ፡ እፅፍ ፡ ድርብ ፡ ክብር ፡ ያገኛሉ ። ግፍ ፡ የተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ታን ፡ ያገኛሉ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ እኔን ፡ የካዱ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ይወርዳሉ ፡ (ይወድቃሉ) ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያለሐኬት ፡ በስሜ ፡ ያመኑ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ። እኔንም ስላመኑ ፡ በስሜ ፡ ስለአስተማሩ ። እፅፍ ፡ ድርብ ፡ ክብር ፡ እሰጣቸዋለሁ ። በስሜ ፡



ያላስተማሩትን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ያልቃል ፡ የማይባል ፡ መከራ ፡ ያገኛቸዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክረምት ፣ በጋ ፡ ዘር ፣ መከር ፣ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አሳብ ፡ የለም ። መውለድ ፡ መዋለድ ፣ ጥል ፣ ክፉ ፡ ነገር ፣ የለም ። ይህ ፡ ወዳጄ ፡ ነው ፣ ይህ ፡ ጠላቴ ፡ ነው ፣ ማለት ፡ የለም ፣ ምድርን ፣ ሰማይን ፣ አድ ሳቸዋለሁ ። መላእክት ፡ ወዳጆቼ ፣ ጻድ ቃን ፡ ወንድሞቼ ፣ ሰማዕታት ፡ በኔ ፡ ያመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጣሉ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ መቼም ፡ ድረስ ፡ ያልፉል ፡ ይጠፉል ፣ ያልቃል ፣ ይደቃል ፣ አይባልም ።

የጌታችን ፡ የመድኀኒታችን ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ቸርነቱ ፣ ይቅርታው ፡ ይደ ረግልን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ አሜን ።